

*በባቡር ላይ የተቀመጠ አሽከርካሪ ስእል*

## Title VI ምንድን ነው?

የ1964 የሲቪል መብቶች ህግ Title VI ማንኛውም የፌደራል የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ፕሮግራሞችን በሚጠቀሙበት ወቅት ግለሰቦችን በዘር፣ በቀለምና በብሔር ላይ የተመሰረተ መድልዎ የሚከላከል የፌዴራል ሕግ ነው።

## በTitle VI መሰረት መድልዎ ምን ማለት ነው?

በTitle VI ስር የሚደረግ መድልዎ አንድ ግለሰብ ወይም የተወሰኑ የሰዎች ቡድን በዘራቸው፣ በቀለማቸው ወይም በብሔር ማንነታቸው ከሜትሮ የህዝብ ጥቅም ወይም አገልግሎት ሲነፈጉ ሊከሰት ይችላል።

---

‹‹በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለ ማንም ግለሰብ በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ማንነት የተነሳ ከፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግለት ፕሮግራም ወይም ተግባር ውስጥ ከመሳተፍ፣ ጥቅማጥቅሞችን ከማግኘት መከልከል ወይም መድልዎ ሊደረግበት አይገባም።›› (ህትመ. L. 88– 352, Title VI, §601, July 2, 1964, 78 Stat. 252)።

---

# እኛ ማን እንደሆንን

## የእኩል የስራ እድል ቢሮ (Office of Equal Employment Opportunity, OEEO)

የእኩል የስራ እድል ቢሮ (Office of Equal Employment Opportunity, OEEO) የፍትሐ ብሔር መብቶች ሕጎችን በማክበር በWMATA መመሪያዎች የተገለጹትን ሁሉንም መስፈርቶች የማሟላት ኃላፊነት አለበት።

OEEO ለሰራተኞች ወይም WMATA የማይሟገት ገለልተኛ ቢሮ ነው። በTitle VI ላይ ስላለዎት መብቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የTitle VI ቅጽ የታተመ ቅጂ ለመጠየቅ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ እባክዎ የሚከተለውን ያነጋግሩ፦

## Title VI ተገዢነት፣ የእኩል የስራ እድል ቢሮ (Office of Equal Employment Opportunity, OEEO)

ስልክ፦ 202 962-2582
ኢሜይል: title.vi.complaint@wmata.com
ድረገጽ፦ www.wmata.com


ተጨማሪ መረጃ

በመረጡት ቋንቋ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ በ **202 637-7000 (TTY 202 638-3780)** ያነጋግሩን።

## የTitle VI ቅሬታ ለዩኤስ የትራንስፖርት መምሪያ ለማቅረብ መምረጥ ይችላሉ፦

U.S. Department of Transportation
Federal Transit Administration's Office of Civil Rights
1200 New Jersey Avenue, 5th Floor
Washington, DC 20590

**ዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን**
**የአካባቢ ትራንዚት ባለስልጣን**
**300 7th Street SW**
**Washington, DC 20024**




*ደንበኞችን የሚረዳ የጣቢያ አስተዳዳሪ*

# የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ትራንዚት ባለስልጣን

**የ1964 የሲቪል መብቶች ህግ Title VI**

**ለህዝብ ማስታወቂያ**




*የRiggs Road Line ሜትሮባስ ጥናት - የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ*

## የTitle VI ፖሊሲ መግለጫ

የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ትራንዚት ባለስልጣን (Metro) ማንም ግለሰብ ከአገልግሎቶቹ ጥቅማጥቅሞች ውስጥ ከመሳተፍ እንዳይገለል ወይም እንዳይከለከል አሊያም በሌላ መልኩ በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ማንነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ እንዳይደርስበት፣ በተሻሻለው የ1964 የዜጎች መብቶች ህግ Title VI እንደተመለከተው ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።

ለዚህ መሳካት፣ የሜትሮ ዓላማው የሚከተሉት ነው፦

- የትራንስፖርት አገልግሎት ደረጃ እና ጥራት ከመድልዎ በጸዳ መልኩ መሰጠቱን ማረጋገጥ፤
- ዝቅተኛ እና አስተኛ ገቢ ባላቸው ሕዝቦች ላይ የሚደርሱ ፕሮግራሞችና ተግባራት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን ጨምሮ፣ እንደአግባቡ ያልተመጣጠነ ከፍተኛ እና ጎጂ የሆኑ የሰው ልጅ ጤና እና የአካባቢ ተጽኖዎችን መለየትና መፍትሄ መስጠት፤
- በሕዝብ ማመላለሻ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የዘር፣ ቀለም ወይም ብሔር ማንነትን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ሙሉ እና ፍትሃዊ ተሳትፎን ማሳደግ፤
- ከፕሮግራሞች እና አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ህዝቦች የሚጠቅሙ ጥቅማጥቅሞችን መንፈግን፣ መቀነስም ወይም ማዘግየትን መከላከል፤
- የተገደበ ወይም የእንግሊዝኛ ችሎታ የሌላቸው ግለሰቦች ለፕሮግራሞች እና ለእንቅስቃሴዎች ትርጉም ያለው መዳረሻ እንዳላቸው ማረጋገጥ።

## ውስን እና እንግሊዘኛ ችሎታ የሌላቸው (LEP/NEP) ግለሰቦች

ውስን እና የእንግሊዝኛ ችሎታ የሌላቸው (LEP/NEP) እንግሊዝኛ ዋና ቋንቋቸው ያልሆነላቸውን እና እንግሊዝኛን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር ወይም የመረዳት ችሎታ ውስን ወይም ጭራሽ የሌላቸው ግለሰቦችን ያመለክታሉ። ለዩናይትድ ስቴትስ የሕዝብ ቆጠራ የእንግሊዝኛ ቋንቋን ብዙ መናገር እንደማይችሉ አሪፖርት ያደረጉ ሰዎችን ያካትታል።

የሜትሮ ቋንቋ እርዳታ ዕቅድ በሜትሮ ድረ-ገጽ ላይ የሚገኝ ነው።

በመረጡት ቋንቋ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ በ **202 637-7000 (TTY 202 638-3780) ያነጋግሩን።**

## Title VI የቅሬታ ሂደት

### እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል

በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ላይ የተመሰረተ አድልዎ እንደደረሰብዎት ካመኑ፣ የአድሎአዊ ድርጊት ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ የTitle VI ቅሬታን ለሜትሮ ማቅረብ ይችላሉ።

የተፈረመበት ቅሬታ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

- ስም፣ ኢሜይል አድራሻ እና ስልክ ቁጥር
- የተጠረጠረውን አድሎአዊ ድርጊትና ለምን አድልዎ እንደደረሰብዎት የሚያምኑበትን መግለጫ (በተቻለ መጠን ብዙ መረጃዎችን ያካትቱ)
- ስም(ሞች) እና የእውቂያ መረጃ፣ ከታወቀ የእርስዎን ውንጀላ(ዎች) ለመደገፍ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሜትሮ ሊያነጋግረው የሚችል ማንኛውም ግለሰብ፤ እና ፊርማዎ።

በዚህ ብሮሹር ጀርባ ላይ ባለው አድራሻ ቅሬታዎን ለሜትሮ ይላኩት።

## ቅሬታዬ ምን ይሆናል?

ቅሬታው እንደደረሰ በደንበኛ ግንኙነት አስተዳደር የውሂብ ቋት ውስጥ ይመዘገባል እናም ለመርማሪ ይመደባል።

ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች በተቀበለው መሰረት፣ OEEO በደረሰው በ90 ቀናት ውስጥ የTitle VI ቅሬታን ይመረምራል። መርማሪው በOEEO ዳይሬክተር የሚገመገም ረቂቅ የጽሁፍ ምላሽን ያዘጋጃል። የOEEO ዳይሬክተር የመጨረሻውን ውሳኔ በመወሰን ለቅሬታ አቅራቢው የመጨረሻውን ምላሽ ያፀድቃል።

ተጨማሪ መረጃ መቀበል ወይም በአንድ ጊዜ ለሜትሮ እና ለውጭ አካል ቅሬታ ማቅረብ የቅሬታውን አፈታት ጊዜ ሊያራዝም ይችላል። ቅሬታ አቅራቢው ለተወሰነ ቀን የተጠየቀውን መረጃ መስጠት ካልቻለ፣ አስተዳደራዊ መቋረጥ ወይም የቅሬታ አፈታት መዘግየት ሊያስከትል ይችላል።

ስለ ሜትሮ ከአድልዎ ነፃ መሆን ግዴታዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ወደ OEEOHotline@wmata.com መልዕክት ይላኩ።